በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ 208950

ግንቦት 3 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ እቴነሽ አሰፋ ወኪል መኮንን በቀለ ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ መሰረት መላኩ
3ኛ. ወ/ሮ ማሚቴ መላኩ
4ኛ. ወ/ሮ ደስታ መላኩ
5ኛ. ወ/ሮ ሙሉ መላኩ
6ኛ. አቶ ለማ መላኩ
7ኛ. አቶ ታመነ መላኩ
} ጠበቃ ደጀኔ ገበየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ በላይነሽ አሰፋ -- ጠበቃ ደረጀ ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች በቀን 08/10/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 66466 በቀን 04/02/2012 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243751 በቀን 03/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው ከ2ኛ-7ኛ የተዘረዘሩ አመልካቾች ባቀረቡት ክስ ሲሆን የአሁን ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ፤ እንዲሁም የአሁን 1ኛ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ከሳሾች በቀን 03/11/2010 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ወ/ሮ ቦጋለች ሺበሺ አያታችን ሲሆኑ በመ/ቁ 67546 በቀን 05/03/2010 ዓ.ም የሟች አባታችን መላኩ ወ/ሰማንያ ተተኪ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁን 1ኛ አመልካቸ) ደግሞ የሟች እናታቸው ልጅና ወራሽ ናቸው፡፡ ሟች ወ/ሮ ቦጋለች ሺበሺ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ቀበሌ 16 የቤ/ቁ 325 የተመዘገበ ቤት ነበራቸው፡፡ ከሳሾች በጋራ 25% ለእያንዳንዳችን ከሳሾች ደግሞ 1/24ኛ ድርሻ፤ እንዲሁም 2ኛ ተከሳሽ 25% ድርሻ አለን፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ሟች በቀን 11/08/1996 ዓ.ም ኑዛዜ አድርገዋል በማለት በመ/ቁ 07365 በቀን 07/03/2010 ዓ.ም ኑዛዜ ማረጋገጣቸውን በ02/11/2010 ዓ.ም ተረድተናል፡፡ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች ወ/ሮ ቦጋለች ሺበሺ ካለመሆኑም በላይ ኑዛዜው በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ በተለይ በፍ/ህ/ቁ 880 እስከ 897 የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች አሟልቶ የተዘጋጀ ስላልሆነ በፍ/ህ/ቁ 2008 መሰረት የፊርማ ምርመራ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን 1ኛ ተከሳሽ ተደረገልኝ የሚሉትን በተመለከተ ጠቅላላ ኑዛዜ ለመሆኑ መረዳት ይቻላል፤ ከሳሾች እና 2ኛ ተከሳሽ የሟች ወደ ታች የሚቆጠሩ ወራሾች በመሆናቸው ከወራሽነት በግልጽ አልተነቀሉም፡፡ ቤቱ በጠቅላላ ኑዛዜ 2ኛ ተከሳሽ ተሰጥቶኛል እያሉ በመሆኑ ኑዛዜው እውነተኛ ቢሆን እንኳ 1ኛ ተከሳሽ እንደ ሟች ልጅ ተቆጥረው የመውረስ መብት ይሰጣቸዋል እንጂ ከሳሾች እና 2ኛ ተከሳሽ ከውርስ ለመንቀል አያስችልም፡፡ ስለሆነም ሟች ወ/ሮ ቦጋለች ሺበሺ አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የፊርማ ምርመራ በፌደራል ፎረንሲክ መምሪያ እንዲሁም ከህግ መመዘኛዎች አንጻር ከታየ በኋላ ኑዛዜው እንዲሰረዝ እና ቤቱ በሐራጅ ወይም በስምምነት እንዲሸጥ ተደርጎ ከዚያ የሽያጭ ገንዘብ ላይ 1ኛ ተከሳሽ አንድ ክፍል ሰርቪስ ቤት የሰሩበት ገንዘብ በመሀንዲስ ተገምቶ ከተቀነሰ በኋላ ከዚህ ገንዘብ ለእያንዳንዱ ከሳሽ 1/24ኛ እንዲሁም ለ2ኛ ተከሳሽ 1/4ኛ ክፍያ እንዲፈጸም፡፡ ይህ ታልፎ ኑዛዜው ህጋዊ ነው ቢባል ቤቱ በሐራጅ ወይም በስምምነት እንዲሸጥ ተደርጎ 1ኛ ተከሳሽ አንድ ክፍል ሰርቪስ ቤት የሰሩበት ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ 2/3ኛ ለከሳሾች (ለእያንዳንዳቸው 1/36ኛ) እንዲሁም ለ2ኛ ተከሳሽ 1/6ኛ ክፍያ እንዲፈጸም በማለት ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) በቀን 27/11/2010 ዓ.ም በሰጡት መልስ በኑዛዜው ላይ ያለውን ፊርማ በማስመርመር አልያም በኑዛዜው ላይ ያሉትን ምስክሮች በማስቀረብ ሟች በኑዛዜው ላይ መፈረም አለመፈረማቸውን እና ኑዛዜው በህግ አግባብ መደረግ አለመደረጉን በማጣራት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መከራከሪያው ውድቅ እንዲደረግ፤ በመ/ቁ 07365 ኑዛዜው ላይ የተፈጸመ አንዳች የፎርም ችግር አለመኖሩን በማረጋገጥ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኛችንን ማከራከር ስለማይገባ ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ፡፡ ኑዛዜው ሟች በነጻ ፈቃዳቸው በሙሉ ጤና ላይ ሆነው ሲደረግ አይተው ማረጋገጣቸውን በእማኝነት በሰነዱ ላይ በመግለጽ ማረጋገጣቸውን ከሰነዱ መረዳት ይቻላል፡፡ ከሳሾች ከኑዛዜው በዝምታ ተነቅለናል እንጂ በግልጽ ተነቅለናል በማለት አልጠየቁም፤ 2ኛ ተከሳሽ በዝምታ አልተነቀሉም ድርሻቸው ተመልክቷል፤ ከሳሾችም ሟች በግልጽ ምክንያታቸውን ገልጸው ለአባታቸው የሚደርሰውን ብር 20,000.00 (ሀያ ሺህ ብር) ከ1ኛ ተከሳሽ ላይ እንዲሰጣቸው የተናዘዙ በመሆኑ ከውርስ በዝምታ አልተነቀሉም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ፡፡ ሟች ወ/ሮ ቦጋለች ባለመብት የሆኑት በይዞታው ውስጥ የሚገኝ ትልቁ መኖሪያ ቤት ግማሽ እና የ3 ክፍል ሰርቪስ ቤት ከነማዕድ ቤቱ ግማሽ መሆኑን በግልጽ ኑዛዜያቸው ላይ የገለጹ እና ይህም ቃላቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ 938(2) መሰረት እውነት ነው ተብሎ መወሰድ የሚገባው በመሆኑ ሟች ይህንን ኑዛዜ ባደረጉበት ወቅት 1ኛ ተከሳሽ የገነባሁት አንድ የሰርቪስ ቤት እና ከኑዛዜ በኋላ በራሴ ገንዘብ ሟች ሳይቃወሙኝ የሰራሁት ቤቶች እና መገልገያዎች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1179(1) መሰረት የግሌ በመሆኑ ከሳሾች እንደሚሉት ግምት ወስጄ የምሄድበት ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ ሟች ባደረጉት ኑዛዜ በቂ ምክንያቶችን በመግለጽ ያላቸውን ሀብት በኑዛዜ አደላድለዋል፤ ስለሆነም ኑዛዜው ህጋዊ መሆኑን እና ምንም አይነት የፎርማሊቲ ችግር የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ የከሳሾችን አቤቱታ የማይቃወሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የሟች ፊርማ እንዲመረመር ፊርማዎች ተሰባስበው እንዲቀርቡ ለግራ ቀኝ ትዕዛዝ ቢሰጥም የተሟላ ፊርማ ማቅረብ ባለመቻላቸው ትዕዛዙ ታልፏል፡፡ ሟች ሚያዚያ 08/1996 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ መሰረት ለከሳሾች አባትና እና ለ2ኛ ተከሳሽም የተናዘዙበት ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ተችሏል፡፡ የኑዛዜው መኖር በምስክሮችም የተረጋገጠ ሲሆን ስለመነበቡም ሆነ ስለፊርማ በተመሳሳይ ምስክርነት የተረጋገጠ በመሆኑ የከሳሾች ክርክር ውድቅ ተደርጓል፡፡ ኑዛዜው በ1996 ዓ.ም የተደረገ ሲሆን የከሳሾች አባትና 2ኛ ተከሳሽ ሊደርሳቸው የሚገባውን መጠን በምንመለከትበት ወቅት ለ2ኛ ተከሳሽ ቀድሞ ይዘውት የነበረውን ቤት እና 10,000.00 (አስር ሺህ) ብር በተጨማሪ ተናዝዋል፡፡ ለከሳሾች አባትም ቢሆን 20,000.00 (ሀያ ሺህ) ብር መስጠታቸው ከግዜው ጋር ሲታይ ከውርስ ሀብቱ ከሚደርሳቸው 1/4ኛ በታች መሆኑን ከሳሾች አላረጋገጡም፤ ቤቱም ከሳሾች ገምተው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ካቀረቡት 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ብር አንጻር ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ አኳያ በሰበር መ/ቁ 18394፣ 50901፣ 47622፣ 54385 እና 55648 ከተሰጡ ውሳኔዎች አንጻር ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ህጋዊ ነው፤ ኑዛዜው ላይ በሰፈረው አግባብ ድርሻቸው ከሚሰጣቸው በቀር ቤቱ በሀራጅ የሚሸጥበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ችሎትም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት ማመልከቻ በስር ክርክራቸው አንጻር ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ተሰርዞ መኖሪያ ቤቱ በሐራጅ ወይም በስምምነት እንዲሸጥ ተደርጎ ከዚህ የሽያጭ ገንዘብ ላይ ተጠሪ ሰርቪስ ቤት የሰሩበት ገንዘብ በመሀንዲስ ተገምቶ ከተቀነሰ በኋላ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ግማሹ ድርሻ ከ2ኛ-7ኛ ለተጠቀሱ አመልካቾች 1/24ኛ እንዲሁም ለ1ኛ አመልካች 1/4ኛ ክፍያ እንዲፈጸም፡፡ ይህ ታልፎ ኑዛዜው ህጋዊ ነው ቢባል መኖሪያ ቤቱ በሐራጅ ወይም በስምምነት እንዲሸጥ ተደርጎ ተጠሪ አንድ ክፍል ሰርቪስ ቤት የሰሩበት ገንዘብ ከተቀነሰ በኋላ ከዚያ የሽያጭ ገንዘብ 2/3ኛ ለተጠሪ ለእያንዳንዳቸው ከ2ኛ-7ኛ አመልካቾች ደግሞ 1/36ኛ እንዲሁም ለ1ኛ አመልካች 1/6ኛ ክፍያ እንዲፈጸም በማለት ማመልከቻቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት ኑዛዜው ህጋዊ ነው በማለት በኑዛዜ መሰረት የተናዘዙትን ገንዘብ አመልካቾች እንዲካፈሉ የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በውሳኔው የተፈጸመ የማስረጃ ምዘናም ሆነ የህግ ስህተት የሌለ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት አቅርበዋል፡፡ አመልካቾችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለሰበር ችሎቱ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት መዝገቡንም አስቀርበን ተመልክተናል፡፡

መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው ከ2ኛ-7ኛ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ እና 1ኛ አመልካችም ደግፈው የተከራከሩት ሟች ወ/ሮ ቦጋለች ሺበሺ በቀን 11/08/1996 ዓ.ም አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም፤ ኑዛዜውም

በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ በተለይ በፍ/ህ/ቁ 880 እስከ 897 የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች አያሟላም፤ ስለሆነም የፊርማ ምርመራም ተደርጎ ኑዛዜው እንዲሰረዝ እና በድርሻችን እንድንከፋፈል። ይህ ታልፎ ኑዛዜው ህጋዊ ነው ቢባል ተጠሪ ተደረገልኝ የሚሉት ጠቅላላ ኑዛዜ በመሆኑና እኛም የሟች ወደ ታች የምንቆጠር ወራሾች ስለሆን ከወራሽነት በግልጽ አልተነቀሉም ተብሎ ቤቱ እንዲሸጥ ተደርጎ በድርሻችን እንድንከፋፈል በሚል የቀረበ ነው። ተጠሪ በበኩላቸው ኑዛዜው ህጋዊ መሆኑን እና ምንም አይነት የፎርማሊቲ ችግር የሌለበት መሆኑን፤ እንዲሁም ሟች ባደረጉት ኑዛዜ በቂ ምክንያቶችን በመግለጽ ያላቸውን ሀብት ያደላደሉ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል።

በመሰረቱ ኑዛዜ የተናዛዡ የግል ሥራ ሲሆን በጥብቅ ስርዓት እንዲከናወንም ይጠበቃል። ኑዛዜው የተናዛዥ የግል ሥራ መሆኑንና በጥብቅ ሥርዓት እንዲከናወን በሕጉ የተመለከተውም ተናዛዡ በነፃ ፈቃድ እና ፍላጎት ኑዛዜ ለማድረግ እንዲችል ለማስቻል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕግ 857 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል።

ህጉ በቀዳሚነት እውቅና የሰጠው የኑዛዜ አደራረግ ሥርዓት ግልጽ ኑዛዜ የሚያሰኘው ነው። የዚህ ዓይነት ኑዛዜ ተናዛዡ እየተናገረ በማንኛውም ሌላ ሰው ወይም በተናዛዡ በራሱ የሚፃፍ፤ በአራት ምስክሮች ፊት አልያም በውል አዋዋይ ፊት ከሆነ ሁለት ምስክሮች ባሉበት ሁኔታ ሊከናወን እንደሚችል፤ ምስክሮችና ተናዛዡ ወዲያው ሊፈርሙበት እንደሚገባ ሁሉ የፍ//ሕግ ቁጥር 881 እና 882 ይዘት ያመለክታል። ኑዛዜ በአራት ምስክሮች ፊት ሲደረግ በግልጽ ስለመነበቡም አመላካች ቃል ሊኖር እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 ላይ ተመልክቷል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች በአከራካሪው ኑዛዜ ላይ ያለው ፊርማ የሟች አይደለም በፎረንሲክ ይመርመር ቢሉም በስር ፍርድ ቤት በዳኝነት ጥያቄው መሰረት የሟች ፊርማ እንዲመረመር ፊርማዎች ተሰባስበው እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቶ የተሟላ ፊርማ ማቅረብ ባለመቻሉ ምክንያት ምርመራ ሊደረግ እንዳልቻለ በማረጋገጥ ታልፏል። ኑዛዜው በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አያሟላም የተባለውን በተመለከተም ሟች ሚያዚያ 08/1996 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ መታየቱን፣ በህጉ አግባብ መደረጉን፣ ኑዛዜው ስለመነበቡም ሆነ ስለፊርማ ሁሉ በተመሳሳይ ምስክርነት ቃል የተረጋገጠ መሆኑ ፍሬ ነገርና ማስረጃ የማጣራትና የመመዘን በህጉ ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል። እኛም የስር ፍርድ ቤት መዝገብን አስቀርበን አከራካሪውን ኑዛዜ እንደተመለከትነው ህጉ የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ ተከትሎ የንስሀአባታቸውን ጨምሮ በአራት ምስክሮች ፊት መደረጉን ተመልክተናል። በመሆኑም ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ አመልካቾች ፊርማ እንዲመረመር እና ኑዛዜው

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የህጉን ፎርማሊቲ አያሟላም ተብሎ ፈራሽ እንዲደረግ ያቀረቡት ክርክር ውድቅ እንዲሆን መወሰኑ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የኑዛዜው ሰነድ አፈፃፀም ሥርዓት አንፃር ጉድለት የለውም ሕጋዊ ነው ከተባለ ተጠሪ ተደረገልኝ የሚሉት ጠቅላላ ኑዛዜ በመሆኑና እኛም የሟች ወደ ታች የምንቆጠር ወራሾች ስለሆን ከወራሽነት በግልጽ አልተነቀሉም ተብሎ ቤቱ ተሸጦ በድርሻችን እንድንከፋፈል በሚል አመልካቾች ከሥር ፍ/ቤት ጀምሮ በአማራጭ ያቀረቡትንም ክርክር መርምረናል፡፡ በመሠረቱ የወራሽነት መብት ከኑዛዜ ወይም ከሕግ የሚመነጭ ነው፡፡ ቀዳሚው ሟቹ በሚያደርገው ህጉን የተከተለ ኑዛዜ ሀብቱን የሚያደላድል ሲሆን የኋው በተለያየ ምክንያት የማይፀና ሲሆን ከሕግ የሚመነጨው የወራሽነት መብት በተወላጅነት ወይም ከሟቹ ጋር ባለው የሥጋ ዝምድና የሚገኝ በመሆኑ ውርሱም በዚህ አግባብ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ሟች ሚያዚያ 08/1996 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ከአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸውን ድርሻ ለይተው ለተጠሪ ብቻ ሳይሆን ከ2ኛ-7ኛ ለተጠቀሱት አመልካቾች አባት እና ለ1ኛ አመልካች ተናዘዋል፡፡ ፍሬ ጉዳዩን የሚመለከተው የስር ፍርድ ቤት ካሳለፈው ውሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለው ለ1ኛ አመልካች አስቀድሞ ተላልፎላቸዋል የተባለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት እና 10,000.00 (አስር ሺ.ህ) ብር በተጨማሪ ተናዘዋል፡፡ ከ2ኛ-7ኛ ለተጠቀሱት አመልካቾች አባት ደግሞ 20,000.00 (ሀያ ሺ.ህ) ብር የተናዘዙ ሲሆን ይህም ኑዛዜ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ አንጻር ሲታይ ከውርስ ሀብቱ ከሚደርሳቸው 1/4ኛ በላይ ጉዳት እንዳደረሰባቸው አመልካቾች እንዳላረጋገጡ፤ በክሱ ቤቱን ገምተው ካቀረቡት 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ.ህ) ብር አንጻር ሲታይም ክርክራቸው ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ በማረጋገጥ ወስኗል፡፡

ይህ የስር ፍርድ ቤቶች የተቀበሉት የፍሬ ነገር መደምደሚያ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ለሆኑት ልጆች ሊደርሰው ከሚገባው የውርስ ሀብት መጠን ከአንድ አራተኛ በታች እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑን የማያረጋግጥ በመሆኑ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ሟች ፈቃዳቸውን በገለፁበት ኑዛዜ መሰረት እንዲከፋፈሉ መወሰኑ ከፍሲል የተጠቀሱትን የህጉን ድንጋጌዎች እንዲሁም የፍ/ብ/ህጉን አንቀጽ 910፣ 912፤ 913፤ 938፤ 939 እና 1123 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ፤ በውጤት ደረጃም የሚነቀፍ አይደለም ከሚባል በቀር ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 66466 በቀን 04/02/2012 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243751 በቀን 03/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በዚህ መዝገብ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. የሥር ፍ/ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም